DC Public Library

# Next Libris

## የተቋማት መሪ ፕላን
## 2021-2030



የColumbia (ኮሎምቢያ) ግዛት የህዝብ ቤተመጻህፍት የሚኖሩበት ቦታ፣ ገቢያቸው ወይም የትምህርት ደረጃቸውን ግምት ውስጥ ሳያስገባ የሁሉንም ኗሪዎች ፍላጎት ለመደገፍ የሚተጋ ቁልፍ የመማሪያ ተቋም ነው።

*Next Libris*፣የDC የህዝብ ቤተመጽሀፍት ተቋማት መሪ ፕላን፣ ቤተ መፃህፉ የከተማውን የህዝብ ቤተመጽሐፍቶች ለመጠበቅ ያለውን ትጋት ብቻ ሳይሆን፣ ለአዲስ አጠቃቀሞች ለማስተካከል እና ብዛት ያላቸው ኗሪዎች ይህን አስፈላጊነቱ እየጨመረ ያለ የህብረተሰቡ ህይወት ሞተር የሆነውን፣ ለማሳደግ እና ተደራሽ እንዲሆን ስትራቴጂክ እድሎችን መፈለግ እንደሚያስፈልግ ይገልጻል። ፕላኑ የመጣው ቤተመጽሀፉ የ10 አመት ትራንስፎርሜሽን ለማጠናቀቅ በሚቃረብበት ሲሆን ከ26ቱ ቤተመጽሀፍት 24 በ2024 አዲስ ወይም መሉ በሙሉ ዘመናዊ ይሆናሉ፣ ይህም የግዛቱ ማእከላዊ ቤተመጽሀፍ የሆነውን የ Martin Luther King Jr. Memorial Library (የማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር የመታሰቢያ ቤተመጽሀፍ) ያካትታል።

የDC ቤተመጽሀፍ የተቋማት መሪ ፕላን ያዘጋጀው ለሚቀጥሉት 10 አመታት እና ከዚያ በላይ ተቋማዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ስትራቴጂውን ለመምራት እንዲረዳው ነው። ትልቅ ህልም ያለው ነው እና ቤተመጽሀፉ ወደፊት፣ አሁን ካለው የበለጠ ብዙ ናሪዎችን በበለጠ ፍትሀዊነት ማገልገል እንዳለበት ሀሳብ ያቀርባል። ቤተመጽሀፎች ለግለሰብ የማህበረሰብ ፍላጎቶች ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጎ በመቅረጽ እና እየተስፋፋ ያለውን የከተማ ፍላጎቶች እንዲያሟላ ሲስተሙን በማሳደግ ቤተመጽሀፉ ይህን ያሳካል።

*Next Libris* አሁን ሥራ ላይ ያለ እና አዲስ መረጃ ሲኖር የሚሻሻል ሰነድ ነው፤ ይህም ቤተመጽሀፉ ለተለዋዋጭ ሁኔታዎች እና እድሎች ምላሽ እንዲሰጥ ያስችለዋል። እቅዱ የተዘጋጀው ከCOVID-19 ወረርሽኝ በፊት ነው፣ እና ይህ በከተማው አገልግሎቶች ላይ የረጅም ጊዜ ጉልህ ተጽእኖዎች ሊኖረው እንደሚችል እናውቃለን።

**ዋና ማጠቃለያ**



*የBenning (ቤኒንግ) ቤተመጽሀፍ ፎቶ፣ Davis Brody Bond (ዴቪስ ብሮዲ ቦንድ)*

## የተቋማት መሪ ፕላን ግቦች

የተቋማት መሪ ፕላን ሶስት ግቦች አሉት። እነዚህ ግቦች ቤተመጽሀፉ ለሚቀጥለው አስር አመት ያለውን የኢንቨስትመንት የውሳኔ አሰጣጥ ፍልስፍናን ያሳያሉ። በቤተመጽሀፉ ሰራተኛ በቅድሚያ የተረቀቀው እና በኋላም በማህበረሰቡ ንቁ የተሳትፎ ሂደት የነጠረው፣ ግቦቹ የሚከተሉት ናቸው፣

### ሀብቶችን በብልሀት ማስተዳደር

ቤተመጽሀፉ እያረጁ ያሉ የህንጻ ሲስተሞችን በንቃት በመጠበቅ ያሉትን ተቋማት ጥሩ ጠባቂ ይሆናል።

### በሀላፊነት ዲዛይን ያድርጉ እና ይገንቡ

ቤተመጽሀፉ ለአጎራባች ፍላጎቶች ምላሽ ሰጭ ሆነው እንዲቀጥሉ የህንጻ ውስጣዊ ክፍሎችን በየጊዜው ያሻሽላል።

### ፍትሀዊ በመሆን እና በብልሀት ማደግ

ቤተመጽሀፉ በColumbia (ኮሎምቢያ) ግዛት ውስጥ የበለጠ ፍትሀዊ አገልግሎቶችን ለብዙ ነዋሪዎች ለመስጠት የሚያስችሉ መንገዶችን መፈለግ።

## የእቅድ አወጣጥ ሂደት

ቤተመጽሀፉ የቀድሞ ታሪክ መረጃን ሰብስቧል፣ ዳታውን ተንትኗል እና ያለው ህንጻ የማህበረሰቡን ፍላጎቶች በምን መልኩ እያሟላ እንደሆነ አዲስ እይታ ለማግኘት ባለድርሻ አካላት እና ማህበረሰቡን አሳትፏል። ይህ አካሄድ ቤተመጽሀፉ ነዋሪዎችን በተሻለ ሁኔታ ለማገልገል የሚያስችል አቋም ላይ እንዲሆን የሚያስችለው አጠቃላይ ግኝቶችን እና ምክረሀሳቦች አካቷል።

**የተቋም ሁኔታ ምዘናዎች እና የአሰራር ምዘናዎች**

**የሠራተኛ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ**

**የቤተመጽሀፍ አጠቃቀም እና ሊኖር የሚችለው አጠቃቀም ምዘና**

**ሙሉ እቅዱን ለማንበብ እና ስለእቅድ ሂደቱ የበለጠ ለመማር፣ ይጎብኙ dclibrary.org/dclibraryfuture ።**

# የአሁን ጊዜ የቤተመጽሀፍ ካርታ እና የአገልግሎት ክፍተቶች

## የDC የህዝብ ቤተመጽሀፍ ዛሬ ምን ይመስላል?

የDC የህዝብ ቤተመጽሀፍ በ900,000 ካሬ ጫማ ስፍራ ላይ የሰፈረ የ26 ቤተመጽሀፍት ሲስተም ነው። ከ26ቱ ውስጥ፣ 20 ዎቹ አዲስ ወይም ሙሉ በሙሉ የታደሱ እና ተጨማሪ አራት ደግሞ በፕላን፣ ዲዛይን ወይም ኮንስትራክሽን ሂደት ላይ ናቸው ይህም ማእከላዊ የ Martin Luther King Jr. Memorial (የማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር የመታሰቢያ ቤተመጽሀፍ) ን ያካትታል። ባለፈው አስር አመት የተደረገው የቤተመጽሀፍ ህንጻዎች ማዘመን በመላው ግዛቱ በእያንዳንዱ ቀጠና የነበረውን እጅግ የላቀ የፕሮጀክት አሰጣጥ ጉዞን ያመለክታል።


ሁሉም ባይሆኑም አብዛኛዎቹ ቤተመጽሀፎች በ15,000 እስከ 20,000 ካሬ ጫማ የተሟላ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፣ ይህም ለህጻናት፣ ወጣቶች እና አዋቂዎች የተለየ ቦታ፣ የስብሰባ ክፍሎች፣ የዝግጅት ቦታዎችን እና በሺዎች ለሚሆኑ መጽሀፎች የመደርደሪያ አቅምን ያካትታል። የDC ቤተመጽሀፍ በመላው ከተማ አገልግሎቶቹን ፍትሀዊ በሆነ መልኩ ለማስፋፋት ሲያቅድ፣ በጣም አነስተኛ ቤተመጽሀፍት በአብዛኛው የሚያገለግሉት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ማህበረሰቦችን እንደሆነ ይገነዘባል። ለፍትሀዊነት አልሞ መትጋት ለእነዚህ ማህበረሰቦች ሙሉ የቤተመጽሀፍት አገልግሎት ለመስጠት የተለያዩ መንገዶችን ማሰስ ይጠይቃል።

## በግዛቱ ውስጥ የአገልግሎት ክፍተት እንዳለባቸው የተለዩ ስድስት ስፍራዎች አሉ።

በግዛቱ ውስጥ የተደረገው አጠቃላይ አሰሳ በሌሎች ስፍራዎች ላይ ያሉትን ተመሳሳይ የአገልግሎት ደረጃ የሌላቸው አጠቃላይ ስድስት ጂኦግራፊያዊ ስፍራዎች እንዳሉ ለይቷል። ክፍተቶች የሚከሰቱት በጂኦግራፊያዊ መገለል ፣ በቂ ያልሆነ የትራንስፖርት አማራጮች ወይም በአጠቃላይ የህዝብ ቁጥር እና የቦታ ስፋት መሰረት በቂ ያልሆነ ካፒታል ነው። በአገልግሎት ላይ ክፍተት መኖር አዲስ ቤተመጽሀፍ እንዲኖር የግድ አስፈላጊ ነው ማለት አይደለም።

**የቤተመጽሀፍት የዛሬ ካርታ**

- *ዘመናዊ የተደረገ ወይም አዲስ ግንባታ*
- *ዘመናዊ ያልሆነ*
- *በአሁን ወቅት በዲዛይን ወይም ግንባታ ላይ ያለ*
- *የትናንሽ የአጎራባች ቤተመጽሀፎች*
- *በአገልግሎት ላይ ያሉ ክፍተት*



ምክረሀሳቦች

## ሀብቶችን በብልሀት ማስተዳደር

እያረጁ ያሉ የህንጻ ሲስተሞችን በንቃት በመጠበቅ ያሉትን ተቋማት ጥሩ ጠባቂ መሆን።

- ያሉትን ተቋማት በተቋማት ሁኔታዎች ምዘና ዳታቤዝ መሰረት መጠበቅ
- የChevy Chase (ቼቪ ቼዝ) ቤተመጽሀፍን መልሶ መገንባት

**የሲስተሞች የእድሳት ፕሮጀክቶች፣ 2021-2030**

**1-3 አመቶች**

- Mt. Pleasant (ማውንቴን ፕሌዛንት)
- Shepherd Park (ሼፐርድ ፓርክ)
- Northeast (ኖርዝኢስት)

**4-6 አመቶች**

- Georgetown (ጆርጅታውን)
- Chevy Chase (ቼቪ ቼዝ)*
- Shaw (ሻው)
- Benning (ቤኒንግ)
- Anacostia (አናኮስቲያ)

**7-10 አመቶች**

- Tenley-Friendship (ቴንሊ ፍሬንድሺፕ)
- Petworth (ፔትዎርዝ)
- Francis A. Gregory (ፍራንሲስ ግሪጎሪ)
- Bellevue (ቤልቪዩ)

## በሀላፊነት ዲዛይን ያድርጉ እና ይገንቡ

ለአጎራባች ፍላጎቶች ምላሽ ሰጭ ሆነው እንዲቀጥሉ የህንጻ ውስጣዊ ክፍልን በየጊዜው ማሻሻል።

- የPetworth (ፔትዎርዝ) ቤተመጽሀፍ እድሳት
- የShaw (ሻው) ቤተመጽሀፍ፣ የ Anacostia (አናኮስቲያ) ቤተመጽሀፍ፣ የBenning (ቤኒንግ) ቤተመጽሀፍ፣ የTenley-Friendship (ቴንሊ ፍሬንድሺፕ) ቤተመጽሀፍ እድሳት
- የGeorgetown (ጆርጅታውን) ቤተመጽሀፍ Bellevue (ቤልቪዮ) ቤተመጽሀፍ፣ Francis A. Gregory (ፍራንሲስ ግሪጎሪ) ቤተመጽሀፍ፣ Mt. Pleasant (ማውንቴን ፕሌዛንት) ቤተመጽሀፍ
- የ Rosedale (ሮዝዴል)፣ Deanwood (ዲንውድ)፣ Northwest One (ኖርዝዌስት ዋን)ቤተመጽሀፍ፣ Parklands-Turner (ፓርክላንድ ተርነር) ቤተመጽሀፍ የአሰራር ምዘናዎች*

**የአሰራር እድሳት ፕሮጀክቶች፣ 2021-2030**

**1-3 አመቶች**

- Tenley-Friendship (ቴንሊ ፍሬንድሺፕ)
- Petworth (ፔትዎርዝ)
- Shaw (ሻው)
- Benning (ቤኒንግ)
- Anacostia (አናኮስቲያ)

**4-6 አመቶች**

- Mt. Pleasant (ማውንቴን ፕሌዛንት)
- Georgetown (ጆርጅታውን)
- Francis A. Gregory (ፍራንሲስ ግሪጎሪ)
- Bellevue (ቤልቪዩ)

**7-10 አመቶች**

- Woodridge (ውድሪጅ)
- Northeast (ኖርዝኢስት)

## በብልሀት እና በፍትሀዊነት ማደግ

በColumbia (ኮሎምቢያ) ግዛት ውስጥ የበለጠ ፍትሀዊ አገልግሎቶችን ለብዙ ነሪዎች ለመስጠት የሚያስችሉ መንገዶችን መፈለግ።

**እርከን አንድ**

አሁን ያሉትን የአፈጻጸም ችግሮችን **እና** የአገልግሎት ክፍተቶችን መፍታት

- New Congress Heights (ኒው ኮንግረስ ሄይትስ) ቤተመጽሀፍ
- የShepherd Park (ሼፐርድ ፓርክ) ቤተመጽሀፍ በአዲስ ቀጠና 4 ቤተመጽሀፍ መተካት
- New Eckington (ኒው ኤኪንግተን)/ Edgewood (ኤጅውድ) ቤተመጽሀፍ

**እርከን ሶስት**

ያሉትን የአገልግሎት ክፍተቶችን**ብቻ መፍታት**

- የRosedale (ሮዝዴል) አዲስ የተስፋፋ/ሙሉ አገልግሎት ቤተመጽሀፍ
- የDeanwood (ዲንውድ) ቤተመጽሀፍ አዲስ የተስፋፋ/ሙሉ አገልግሎት

**እርከን ሶስት**

ያሉትን የአገልግሎት ክፍተቶችን **ብቻ መፍታት**

- New Adams Morgan (ኒው አዳምስ ሞርጋን)/ Dupont Circle (ዱፖን ሰርክል) ቤተመጽሀፍ
- የFort Lincoln (ፎርት ሊንከን)/Gateway (ጌትዌይ)/Arboretum (አርቦሬተም) የክፍተት መፍትሄዎችን ማሰስ
- ለCathedral Heights (ካቴድራል ሄይትስ)/ Wesley Heights (ዌስሊ ሄይትስ)/Glover Park (ግሎቨር ፓርክ) የክፍተት መፍትሄዎችን ማሰስ

*ተቋሙ ካልተተካ የእድሳት ፕሮጀክቶች አስፈላጊ ይሆናሉ።



የCleveland Park (ክሊቭላንድ ፓርክ) ቤተመጽሀፍ ፎቶ፣ Joseph Romeo (ጆሴፍ ሮሚዮ)

## የ2019 ስታቲስቲክስ

**3.8M** በአመት የመግቢያ ብዛት

**446K** የሚሰሩ አጠቃላይ አካውንቶች

**944K** የኮምፒውተር ክፍለጊዜዎች

**4.9M** አመታዊ ዝውውር

**24K** የስብሰባ ክፍል ማቆያዎች